# የትግበራ ሁኔታ፦ በሠብአዊነት ቦታ ውስጥ የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደር የለውጥ ሂደት

እንደ የሠብአዊነት ፖሊሲ እና ተግባር ርዕሰ ጉዳይ፣ የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደር (SRM) ንቁ እና እያደገ ያለ ሆኖም ግን ገና ብዙ ያልተጠና የስራ መስክ ነው። ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት፣ ጥቂት ቁጥር ያላቸው አጠቃላይ፣ ሴክተር ተኮር የSRM ትንታኔዎች ታትመዋል፣ ሆኖም ግን አንዳቸውም ቢሆኑ ያለፉትን በርካታ አመታት ጉልህ እድገቶችን ለመሸፈን በቂ እና ወቅታዊ አይደሉም። ይህ ሪፖርት በየጊዜው እያደጉ ካሉ ስጋቶች አንፃር ፍላጎቶችን ለማሟላት ተሰማሚ የዘርፍ አውድ ውስጥ በሠብአዊነት ስራዎች የSRM ውስጥ ያሉትን ወቅታዊ የመፈጸም አቅም፣ አጣብቂኞች እና ተግዳሮቶችን ያብራራል።

ጥናቱ እንደሚያመለክተው የሠብአዊ ድርጅቶች ለአጋጣሚ እና የውስጥ ስሜት መረዳት ሳይተው በተናጥል እና በመቀናጀት የሰሩት ስራ የሰራተኞቻቸውን ደህንነት እና ጥበቃ በተደራጀ መልኩ በቅድመ እርምጃዎች በማጎልበት ጉልህ እድገቶችን ማስመዝገባቸውን አመላክቷል። የአሰራር ስልቶች ተቋማዊነት በጣም ሩቅ ሊሄድ ወይም በተሳሳተ መንገድ ሊተገበር ቢችልም በአጠቃላይ የሠብአዊ ድጋፍ ሰጪዎች ብዙውን ጊዜ ከሕይወት እና ከሞት አደጋ ጋር በተያያዘ ፈታኝ በሆነ አካባቢ እድገት አድርገዋል እናም አደጋን መቀነስ ብቻ እንጂ በጭራሽ ማሰወገድ እንደማይቻል ማወቅ።

በመጨረሻም፣ የSRM ስኬት ወይም ውድቀት የሚለካው በሰለጠኑት ሰራተኞች ብዛት ወይም በተተገበሩ ሂደቶች፣ ወይም በተከሰቱ የደህንነት አደጋዎች ላይ ሳይሆን፣ እርምጃዎቹ በምን ያህል ችግር ውስጥ ላሉ ሰዎች ውጤታማ የሆነ ሠብአዊ ምላሽ እንዳስገኙ ነው።

የምርምር ፕሮጀክቱ ግኝቱን ያገኘው በኮሎምቢያ፣ በመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ዩክሬን፣ ኢራቅ እና ኢትዮጵያ ከተደረጉ ቁልፍ የመረጃ ሰጪ ቃለመጠይቆች፣ የበየነ መረብ የዳሰሳ ጥናት እና ሀገራቱን መሰረት ካደረገ ጥናት ነው።

## ቁልፍ ግኝቶች

- የSRM ስርዓቶች እና አቅሞች ዝግጅት ድርሻ ጉልህ ቢሆንም ግን የተዛባ ነው
- አዳዲስ ስጋቶች እና ተለዋዋጭ የደህንነት ሁኔታዎች የሠብአዊ እርዳታ ተደራሽነትን እና መላመድን ይፈታተናሉ።
- ጥልቅ ልዩነት፦ እየተሰራበት ያለው የአጋርነት ማሳያዎች ሀገራዊ እና ብሔራዊ ድርጅቶች የራሳቸውን የSRM መመሪያ ማዘጋጀት አልቻሉም
- የSRM መመሪያ ቅንጅት፣ ግብዓቶች እና ስልጠና ላይ ጉልህ እድገት መታየት እና ተደራሽነታቸውን የማስፋት አስፈላጊነት
- እጃቸው ካለበት ከታጠቁ ኃይሎች/ተዋናዮች ጋር የመግባባት እና የመተባበር ተግዳሮቶች
- ደህንነትን በግለሰብ ደረጃ ማበጀት፦ የSRM በሰው ላይ ያተኮረ አቀራረብ ማድረግ ላይ የተደረጉ እርምጃዎች

እነዚህ ቁልፍ ግኝቶች በዚህ ማጠቃለያ ላይ በዝርዝር ተብራርተዋል።


# ለእርዳታ ሠራተኞች ደህንነት ማጣት

## በተጎጂዎች መረጃ ላይ ያሉ አዝማሚያዎች

በግጭት አካባቢዎች ያሉ የሠብአዊ እርዳታ ሰጭ ሠራተኞች ከስራ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ይልቅ በጥቃት የመሞት እድላቸው ከፍተኛ ነው። በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ትልልቆቹ ስጋቶች አነስተኛ በሆነ የምላሽ ቀጠናዎች ላይ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆኑ፣ ጉዳቱም በሚያስደነግጥ ሁኔታ ከፍተኛ ነው።

ከ20 ዓመታት በላይ በደህንነት አደጋዎች ላይ ያለው መረጃ እንደሚያሳየው የረዥም ጊዜ የከባድ ጥቃት ጥቃቶች እና ተጎጂዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሆን ይህም እየተሰፋፋ ያለውን ዓለም አቀፍ የሠብአዊ ዘርፍ እና አብዛኛው የሠብአዊ እርዳታ ሥራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች የግጭቶች መስፋፋት እና መጠናከርን የሚያንፀባርቅ ነው።

**ምስል 1:-** የእርዳታ ሰጪ ሠራተኞችን የሚጎዱ ዋና ዋና ጥቃቶች እና ጠቅላላ የተጠቂዎች እና የሟቾች ቁጥር በዓመት፣ 2000-2022 እ.ኤ.አ




## አዲስ ስጋቶች እና ተለዋዋጭ የደህንነት ገጽታዎች

የደህንነት እጦት በአብዛኛው ዐውድ-ተኮር የሆነና እና ዓለም አቀፋዊ አዝማሚያዎችን የማይከተል ቢሆንም፣ የሠብአዊነት ደህንነት ባለሙያዎች አሁን ባለው ሥራቸው እና ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አንዳንድ አጠቃላይ ለውጦችን አስተውለዋል።

| | |
|---|---|
| **ውስብስብ አስጊ ሁኔታዎች** | የመተግበሪያ አከባቢዎች ውስብስብነት እየጨመረ መምጣቱ (ግጭቶች እና ያልተረጋጉ ሁኔታዎች፣ በደካማ ወይም በሌሉ የህግ የበላይነት እና በበርካታ የታጠቁ ተዋናዮች መኖር) የእርዳታ ድርጅቶችን አደጋዎችን የመገመት እና የማስተዳደር አቅማቸውን እያዳከመ ነው። |
| **የዲጂታል አደጋ ስጋቶች** | የዲጂታል አደጋዎች መጨመር፣ የተሳሳተ/ የተሳሳተ መረጃን፣ የሳይበር ወንጀልን እና የዓለም አቀፋዊ አደጋ ስጋቶች መጨመር አሳሳቢ እየሆነ መምጣት እንዲሁም በበይነ መረብ ላይ የሚሰራጩ የጥላቻ መልክቶች በፍጥነት ወደ እውነተኛ ህይወት ስጋቶች ይቀየራሉ። |
| **ወንጀል እና የወንጀል ኢኮኖሚ** | በየደረጃው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የደህንነት ሠራተኞች ሪፖርት በጣም ወንጀል ተስፋፍተው ስጋት ከሆኑት ውስጥ አንዱ ሲሆን የሠብአዊ እርዳታ ሰጭዎች የቦታ እና የህዝብ ተደራሽነትን ከሚቆጣጠሩ የወንጀል ተዋናዮች ጋር የመጋፈጥ ፈተና እየታገሉ ነው። |
| **በትላልቅ ጦርነቶች ውስጥ የሚፈጠር የጎንዮሽ ጥቃት** | ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሠብአዊ እርዳታ ጥረቶች በትልቅቅ ጦርነቶች እና ተያያዥነት ባላቸው ግጭቶች ምክንያት እየተባባሰ የሚሄድ አደጋ ገጥሟቸዋል። |
| **የWagner Group በአፍሪካ መገኘቱ** | ተለዋዋጭ በሆነው የጸጥታ ሁኔታ መሻሻሎች እና ተግዳሮቶች ሁለቱም እያሉ እንደ Wagner Group ያሉ ዓለም-አቀፍ ተዋናዮች የሠብአዊ ሰራተኞች በሚሰሩበት አካባቢ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እያሳደሩ ነው። |
| **የተቀላቀለ ጽንፈኝነት እና የሽግግር ሁኔታ** | ጥናት በተደረገባቸው ሀገራት ሁሉ፣ ድርጅቶች እየተበላሹም ሆነ እየተሻሻሉ ካሉ ለውጦች የደህንነት እና የቀውስ ሁኔታዎች ጋር ለመላመድ ሲታገሉ ያሳያሉ። |

# በሠብአዊ ሰራዎች ውስጥ የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደር እድገት (1/2)

የሠብኣዊ ዘርፍ በተለይ ባለፉት 10 ዓመታት የSRM ሥርዓቶችን እና አቅም በመገንባት ረገድ ጉልህ እድገት አሳይቷል፣ ይህም ከግብረመልስ እና ከገደብ የደህንነት እርምጃዎች ወደ ንቁ" የሚያስችለውን" አደጋ አያያዝ ማስተላለፍን ያካትታል። ይህ አስደናቂ ግስጋሴ ያልተሰተካከለ ሆኖም ግን በዋናነት ዓለም-አቀፍ ተዋናዮችን ተጠቃሚ ያደረገ ነው።

## አሁን ያለው የSRM አወቃቀሮች እና አቅም

ጥያቄ የቀረበላቸው ሁሉም የዓለም-አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች በደንብ የዳበረ የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደር ስርዓቶች አሏቸው። ከዚህ በተቃራኒ የአካባቢው/ብሔራዊ ድርጅቶች የSRM አቅሞቻቸው አሁንም በአግባቡ ድጋፍ ያላገኙ እና በደንብ ያልዳበሩ ናቸው።

ለዓለም-አቀፍ እና ለብሔራዊ/አካባቢያዊ ድርጅቶች አፈጻጸምን ለማሻሻል ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች፦

- የአደጋ ጊዜ እቅድ እና ዝግጅት
- የአደጋ ስጋት ግምገማ
- የSRM የሰራተኞች አፈጻደም አቅም

በዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ፣ የSRM ለሰራተኞች በሚሰጠው ድጋፍ ዓይነት መካከል ልዩነቶች መኖራቸውን እንደቀጠሉ። ዓለም-አቀፍ ሠራተኞች፣ የጸጥታ ሁኔታ አጭር መግለጫዎችን፣ ስልጠናዎችን፣ የህክምና መድህን፣ የህይወት መድህን እና ከአደጋ በኋላ እንክብካቤን ጨምሮ የSRM ድጋፍን ከሀገራዊ ባልደረቦቻቸው ይልቅ የማግኘት እድላቸው ሰፊ ነበር ።

## የአደጋ ስጋት ግምገማ እና ትንተና

ስጋቶችን መገምገም የSRM መሰረት ሲሆን ምክክር ከተደረጉ ድርጅቶች ከSRM ጉዳይ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ሆኖ ተገኝቷል። የደህንነት አደጋ ስጋት ግምገማ አሁን በሴክተሩ ወጥነት ያለው ሂደት እየተደረገ ነው። ጥናቱ ግን ተጨማሪ ውይይት የሚገባቸው ሶስት ዋና ዋና ጉዳዮችን አግኝቷል፦

**መደበኛ የሆኑ የአደጋ አጋት ግምገማዎች የእይታ መሰክን ያጠባሉ?**

በእርግጠኝነት ሊፈጠሩ በሚችሉ ስጋቶች ላይ የሚያተኩሩ የአደጋ ስጋት ግምገማዎች፣ በርቀት ያለ ሆኖም ግን በኋላ ትልቅ ተጽዕኖ የሚኖራቸውን አደጋዎች ብዙ ቦታ ላይሰጧቸው ሊቀሩ ይችላሉ።

**ከውጪ /ከሶስተኛ ወገን በተገኘ ትንተና ላይ መተማመን**

እንዳንድ ጊዜ ለታሰበለት ዓላማ ተስማሚ ላይሆን በሚችል የሶስተኛ ወገን የአደጋ ስጋት ትንተና ላይ የበለጠ የመተማመን አዝማሚያ አለ።

**የአደጋ ስጋት ግምገማ ሂደቶችን መነጣጠል**

ብዙ ድርጅቶች አሁንም ድረስ የደህንነት አደጋ ስጋት ግምገማዎችን እንደ ገለልተኛ እንቅስቃሴ እና የደህንነት የትኩረት ነጥቦች ብቻ አድርገው ይመለከቷቸዋል።

# በሠብአዊ ስራዎች ውስጥ የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደር እድገት (1/2)

**ለደህንነት የሚውል የገንዘብ ድጋፍ**

ለSRM የገንዘብ ድጋፍን በተመለከተ በተለያዩ የእርዳታ ተዋናዮች መካከል ያለው ልዩነት አሁንም አለ።

### ዓለም-አቀፍ ድርጅት

ለጋሾች ከደህንነት ስራዎች በተለይም በከፍተኛ የአደጋ ስጋት ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ውስጥ የገንዘብ ድጋፍን በተመለከተ አዳዲስ ሀሳቦችን ለማስተናገድ ፈቃደኛ ናቸው።

አንዳንድ ጊዜ በድርጅቶች ውስጥ ፕሮግራሙ ሲታቀድ የSRM አስቀድሞ አይተዋወቅም፣ በዚህ የተነሳ የደህንነት ወጪዎች ከበጀት የመቀነስ አደጋ አላቸው።

### የአከባቢው እና ብሔራዊ ድርጅቶች

ለደህንነት ስራ በቂ ያልሆነ እና አልፎ አልፎ (በፕሮጀክት ላይ የተመሰረተ) የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ SRMን ለማዘጋጀት እና ለመተግበር የሚያስፈልጉ ግብአቶች እጥረት ማለት ነው።

የዓለም-አቀፍ ተዋናዮች መስፈርቶች እና የገንዘብ እጥረት የአካባቢያዊ/ብሔራዊ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች(NGO) ለፕሮግራም እና አስተዳደራዊ ወጪዎች ቅድሚያ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል።

### ለጋሾች

ዋና ዋና የሠብአዊ እርዳታ ሰጪ ኤጀንሲዎች SRMን ለመደገፍ እና እንደሁኔታው ተለዋዋጭ የበጀት አወጣጥን ለማመቻቸት ያላቸው ችሎታ እና ፈቃደኝነት ላይ መሻሻል አሳይተዋል።

ለጋሾች ለአካባቢው ተዋናዮች በቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ ባለማድረጋቸው፣ የአከባቢው/ብሔራዊ NGO የSRM ፍላጎታቸውን ማሟላት እንዳይችሉ በማድረግ ላይ ትልቅ ሚና አላቸው።

# የአካባቢው ተዋናዮች እና ብሔራዊ-ዓለም አቀፍ አጋርነት

ምንም እንኳን የዓለም-አቀፉ ማህበረሰብ ለአካባቢያዊነት የማዳደግ ዓላማ እንዳላቸው ቢገለጽም፣ የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደር ዕድገት አንጻራዊ ደረጃ እንደሚያመለክተው የአካባቢው/ብሔራዊ ድርጅቶች ከዓለም አቀፋዊ አቻዎቻቸው በፀጥታ/ደህንነት አደጋ ስጋት አሰተዳደር ስርዓት 20 ዓመታት ያህል ወደኋላ የቀሩ ናቸው። የአካባቢው ተዋናዮች ግንባር ቀደም አቅራቢዎች እንደመሆናቸው መጠን የበለጠ ለአደጋ ስለሚጋለጡ ልዩነቱ በጣም አስቸጋሪ ነው።


## የአካባቢው ተዋናዮች በጥቂት የደህንነት ድጋፍ የተነሳ ከፍተኛ ተጋላጭ ናቸው

ባለፉት ሰባት ዓመታት ብሔራዊ እና በአካባቢው ድርጅቶች የተጎዱባቸው ሰዎች ቁጥር ያለማቋረጥ እየጨመረ የሄደ ሲሆን በ2022 ከዓለም-አቀፍ NGO በእጅጉ በልጧል (የድርጅቶቹ ተጎጂዎች ቁጥር ከ2019 ወዲህ ቀንሷል)።

ያነጋገርናቸው ሁሉም ብሔራዊ ድርጅቶች ሊደርሱባቸው የሚችሉትን የአደጋ ስጋቶች እና የSRM ሠራተኞች እና ተቋማዊ አቅም ያላቸውን ዋጋ ጠንቅቆ የሚያውቁ ቢሆንም በቀላሉ ሊያገኟቸው ግን አልቻሉም። የተንሰራፋ እና ለውጥን የማይቀበል የገንዘብ ድጋፍ ሞዴል መሰረታዊ ድርጅታዊ አቅሞችን እንዳይገነቡ አግዷቸዋል።

በአብዛኛዎቹ አጋርነቶች፣ በSRM ላይ ያለው ትብብር ጥብቅም ሆነ ሁሉን አቀፍም አይደለም እናም ብዙውን ጊዜ በSRM አስተዳደር ስርዓቶች ላይ ላዩን ባለ የአንድ ወገን ግምገማ እና የደህንነት የትኩረት ነጥብ በመሰየም ላይ ብቻ የተገደበ ነው።

**ምስል 6፡-** የእርዳታ ሠራተኛ ተጠቂዎች ቁጥር በድርጅቶች ዓይነት፣ 2011-2022 እ.ኤ.አ




## የተጠያቂነት ስጋት በደህንነት ጉዳይ ትብብር እንዳይኖር አድርጓል?

በዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የደህንነት ባለሙያዎች በአጠቃላይ፣ በአጋር ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች መደበኛ የህግ ሃላፊነት ቢኖርም ባይኖርም የስነ-ምግባር ወይም የሞራል ተገቢውን የጥንቃቄ ግዴታ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው ይስማማሉ። ሆኖም፣ ማንኛውም መደበኛ የሆነ የጥንቃቄ ግዴታ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ እውቅና ተሰጥቶት ከሆነ፣ አንድ ዓለም-አቀፍ አጋር በአካባቢው አጋር ድርጅቶች ላይ ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ተጠያቂ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት እያደገ ነው።

**የጥንቃቄ ግዴታ ሥነ ምግባራዊ ግዴታ**


- የዓለም-አቀፍ ድርጅት የደህንነት ሠራተኞች ለአጋሮች እንዴት ተግባራዊ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ግራ መጋባት እና እርግጠኛ አለመሆን።
- በአጋሮች መካከል በአስፈጻሚዎች ደረጃ ጊዜያዊ የደህነት የጋራ ተሳትፎ።

**የተጠያቂነት ስጋት**

- የአመራር ቡድኖች ለአስፈጻሚ ቡድኖች፣ ከአካባቢያዊ አጋሮች ጋር በፀጥታ ዙሪያ በጣም በቅርበት እንዳይሰሩ አመራር ይሰጣሉ።
- አጋሮችን አለማቅረብ - አደጋን ያለ የመቀነስ አቅም ማስተላለፍ።
- የአጋርነት ተነጻጻሪ ጥቅሞችን በአግባቡ መጠቀም አለመቻል።

## ተደራራቢ እና ያልተቀናጁ የአጋርነት ዝግጅቶች

ጥቂት ቁጥር ያላቸው፣ በደንብ የተመሰረቱ እና የመተግበር አቅም ያላቸው አካባቢያዊ /ብሔራዊ NGO (ብዙውን ጊዜ የSRM ስርዓት ያላቸው ብቸኛ የአገር ውስጥ ተዋናዮች) የበርካታ ዓለም-አቀፍ ኤጀንሲዎች ተመራጭ አጋር ይሆናሉ። በዚህም ምክንያት እነዚህ የአካባቢያዊ /ብሔራዊ NGO በዓለም-አቀፍ አጋሮቻቸው የተቀመጡ በርካታ፣ ያልተቀናጁ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ መስፈርቶችን እና በዓለም-አቀፍ አጋሮቻቸው የተቀመጡ የSRM የሥራ ፍሰቶችን ለማስተናገድ ይገደዳሉ።



# የደህንነት ቅንጅት (1/2)

አንዳንድ ወሳኝ ክፍተቶች አሁንም ቢኖሩም፣ የSRM በዓለም-አቀፍ እና በአካባቢ ደረጃ ያለው መቀኛጀት ጨምሯል፣ የበለጠ ስርዓት ያለውም እየሆነ መጥቷል፣ እንዲሁም በመርሁ ላይም ጥያቄ አይነሳም።

## መደበኛ ያልሆነ ቅንጅት

የዲጂታል የመገናኛ መድረኮች መጨመር ለደህንነት ቅንጅት በረከትም አደጋም ነው። የማህበራዊ ሚዲያ እና የመልእክት መላላኪያ መተግበሪያዎችን በመጠቀም የሠብአዊነት ደህንነት ሠራተኞች ፈጣን መረጃን እንዲቀበሉ፣ እንዲያስተላልፉ እና የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን እና እውቂያዎችን ከዓላማቸው ጋር እንዲስማማ ማድረግ ችለዋል። በሌላ መልኩ እነዚህ ዲጂታል መሳሪያዎች የሚከተሉትን የአደጋ ስጋቶች ያስከትላሉ፦

- የተሳሳተ መረጃ፣ የተዛባ መረጃ እና ስለላ
- የመረጃ መከፋፈል
- አለመረጋጋት

## የቅንጅት ሽፋን ክፍተት

የSRM ትልቁ ተግዳሮቶች በጥናቱ ተሳታፊዎች የተገለጹትን በሠብአዊነት ቦታ ውስጥ ያሉትን ክፍተቶች እና ፍላጎቶችን በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት ይመስላል። የአካባቢው/ብሔራዊ NGO በዓለም-አቀፍ ተዋናዮች ተቀርፀው እና በሚመሩት በስራ ላይ ያሉት በአብዛዎቹ የማቀናጀት ስልቶች ውስጥ ውክልናቸው ዝቅተኛ ነው። በትላልቅ ቀውሶች ወቅት፣ የሠብአዊነት ተዋናዮች በአካባቢ ደረጃ በተለይ በጣም ብዙ እና የተለያዩ ከመሆናቸው የተነሳ አንድም ዓለም አቀፍ የሚመራ ዘዴ ሁሉንም ሊሸፍን እና ሊያገለግል አይችልም። ከዓለም-አቀፍ አሰተባባሪ አካላት ጋር ሊገናኙ የሚችሉ ተጨማሪ፣ ዐውድ-ተኮር የአካባቢ አሰተባባሪ መድረኮችን መደገፍ እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነው።

## መደበኛ ቅንጅት

በሠብአዊነት የSRM ውስጥ የሚከተሉት መደበኛ ቅንጅት እየተካሄደባቸው ካሉት ዋና ዋና ስልቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

### የተባበሩት መንግስታት የደህንነት አስተዳደር ስርዓት (UNSMS)።

- የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች በUNSMS ስር የተቀናጁ ናቸው።
- የተባበሩት መንግስታት የደህንነት እና ጥበቃ መምሪያ(UNDSS) የተለያዩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶችን የSRMን ለመደገፍ እና ለማቀናጀት የተቋቋመ ነው።

### ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ደህንነት ተቋም (INSO)

- INSO በሀገር ደረጃ ዋናው የSRM ማቀናጃ ስልት ነው።
- INSO ደህንነት ተቋም በተገኝባቸው አገሮች ውስጥ NGO እና በተባበሩት መንግስታት ደህንነት/ፀጥታ ጉዳዮች መካከል እንደ አንዱ ዋና ግንኙነት መሰመር ሆኖ ያገለግላል።
- የመድረኩ ደጋፊዎች፣ ከነቃፊዎቹ እጅግ ቢበልጡም፣ የምርምር ቡድኑ ግን አንዳንድ ተደጋጋሚ ትችቶችን ሰምቷል።

### አለም አቀፍ የድርጅቶች የጋራ የደህንነት መድረክ (GISF)

- GISF ለዓለም-አቀፍ ደረጃ ውይይት እና ትብብር፣ መመሪያ፣ የመጀመሪያ ምርምር እና ለSRM ተግባራዊ መሣሪያዎች እና አብነቶች መድረክ ነው።
- የGISF አባልነት ከአንድ ሀገር በላይ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች የተገደበ ቢሆንም፣ የምርምር ውጤቶች እና አንዳንድ ዝግጅቶች ግን ለሁሉም ተዋናዮች ክፍት ናቸው።

# የደህንነት ቅንጅት (2/2)

### ሕይወትን በጋራ ማዳን (SLT)

- ሕይወትን በጋራ ማዳን፣ የተባበሩት መንግስታት እና NGO በደህንነት ስራ ላይ እንዴት እንደሚተባበሩ እና የበለጠ ቅንጅትን መፍጠር እንደሚችሉ የሚያስችል ማዕቀፍ ነው።
- የSLT ዓላማዎች እና ተግባራትን በስፋት አለመረዳት እና የጋራ ግንዛቤ አለመኖር የSLT ጉዳይ ለተባበሩት መንግስታት እና ለዓለም-አቀፍ NGO ተደጋጋሚ የራስ ምታት ምንጭ ነው።

### የአጋር ግንኙነት ደህንነት ቢሮዎች (PLSOs)

- በሀገር ደረጃ የሚንቀሳቀሱ PLSO የአፈጻጸም አጋሮቹን የአሰራር ደኅንነት ለመደገፍ በዩኤስኤይድ ይደገፋሉ።
- PLSO ከአንዳንድ ግብረሰናይ NGO ዘንድ ያለው አቀባበል የተደባለቀ ነው።

### የአለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ደህንነት እና ጥበቃ ማህበር (INSSA)

- INSSA የግለሰቦችን የደህንነት ስጋት አስተዳደር የቴክኒካል ክህሎት ማዳበር ላይ እና ለሠብአዊ የSRM ባለሙያዎች ደግሞ የእውቅና ደረጃዎች ላይ የሚያተኩር መድረክ ነው።

# በSRM ግብዓቶች ላይ ያሉ እድገቶች

ጥናቱ እንደሚያሳየው ባለፉት አስር አመታት በተለይም በዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ በመገልገያ መሳሪያዎች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የአሰራር ሂደቶች እና የስልጠና ግብአቶችን በማዘጋጀት ረገድ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል።

## አደጋ መከታተል

በአለፉት አስርት አመታት ውስጥ የደህንነት አደጋን መከታተል በጣም ተስፋፍቷል፣ እንደ 72% የዳሰሳ ጥናት ምላሽ ሰጪዎች፣ አብዛኛዎቹ የአካባቢው /የብሔራዊ NGO ምላሽ ሰጪዎችን ጨምሮ በድርጅታቸው ውስጥ ዓለም አቀፋዊ ክስተት ሪፖርት ስርዓት መዘርጋታቸውንም ገልጸዋል። በዚህ ረገድ ግልጽ መሻሻሎች ቢኖሩም፣ ቃለመጠይቅ ተደራጊዎቹ ሦስት ዋና ዋና ተግዳሮቶችን ለይተው አውጥተዋል፦

**ፈጻሚ አጋሮችን እና የውል ሰራተኞችን የሚነኩ ክስተቶችን በስርዓት አለመመዝገብ።**

**የሪፖርት አደራርግን ጥራት ማሻሻል አስፈላጊነት።**

**የደረሱ ክስተቶችን አሳንሶ ሪፖርት ማድረግ።**

አብዛኛዎቹ እነዚህ ተግዳሮቶች አዲስ ወይም ያልተጠበቁ አይደሉም፣ እናም በርካታ የስልጠና አቅራቢዎች እና ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ከእነዚህ ስጋቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችን ጠቁመዋል።

ለሰራተኞች እንክብካቤ እና የአዕምሮ ጤና ድጋፍ

የጥናቱ ቡድኑ ብዙ የተለያዩ የአዕምሮ ጤና እና ደህንነት ስጋቶችን የመዘገበ ሲሆን ነገር ግን ለችግሩ ጥቂት ብቻ ተመጣጣኝ የቅነሳ ስርዓት ምሳሌዎችን አግኝቷል። ሆኖም ግን የሰራተኞች እንክብካቤ እና የአዕምሮ ጤና ድጋፍ አሳሳቢነት እውቅና ያገኘና፣ የተለያዩ ድርጅቶች እንዴት በተሻለ ሁኔታ መፍትሄ እንደሚያገኙለት በየጊዜው እየመረመሩ ይገኛሉ።

## ስልጠና

ያለፉት አስርት አመታትም በእርዳታው ዘርፍ በደህንነት ጉዳዮች ማለትም ለጠቅላላ የእርዳታ ሠራተኞች በግል ደህንነት እና ጥበቃ ኮርሶች፣ እንዲሁም በSRM ስልጠና እና ለደህንነት ባለሙያዎች ክህሎት ማዳበር ስልጠና ላይ ከፍተኛ እድገቶችን ታይቷል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የተከሰቱትን መዘጋቶችን ተከትሎ፣ በኦንላይን የሚሰጡ የደህንነት ላይ ኮርሶች ፍንዳታም ተፈጥሯል። ይሁን እንጂ የሚከተሉት ተፈታታኝ ሁኔታዎች አሁንም አሉ፦

**ልዩነቶች**
የአካባቢው/ብሔራዊ ሠራተኞች የግል ደህንነት እና ጥበቃ ስልጠና የማግኘት ዕድላቸው በጣም አነስተኛ ነው፣ በተለይም ለአከባቢ ድርጅት የሚሠሩ ከሆነ።

**ተደራሽነት**
ለአካባቢው ተደራሽ እና ለቋንቋ ተስማሚ የሆነ የደህንነት ስልጠና አለመኖር።

**ውጤታማነት**
በተለያዩ የግል ደህንነት ስልጠና ዓይነቶች ውጤታማነት ላይ ጠንካራ ማስረጃዎች በስፋት አለመኖር።

**ቀጣይነት**
የጥላቻ የአካባቢ ግንዛቤ ስልጠና(HEAT) ኮርሶች በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች በገንዘብም ሆነ በሎጂስቲክስ ተደራሽ ባይሆንም ለደህንነት ስልጠና እንደ ወርቃማ መመዘኛ እየታዩ መጥተዋል የሚለው ስጋት አለ።


**ጥራት**
ከፍተኛ ጥራት እና ሁኔታ ተኮር በሆኑ የHEAT ኮርሶች (በቤት ውስጥ እና በውጭ) እና ዝቅተኛ ጥራት እና አጋጣሚ ጠበቅ በሆኑ ኮርሶች መካከል ሰፊ ልዩነት።

**አግባብነት**
ልዩ ሁኔታዎችን፣ ፕሮግራሞች፣ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ግምት ውስጥ ያሰገባ ስልጠና ከማበጀት ይልቅ በተለመዱ መንገዶች የተፈጠረ፣ ብዙ ጊዜ ውጤቱ የተለመደ፣ አሰልቺ ወይም ለሁሉም ፍላጎቶች የማይተገበር የኮርስ ዲዛይን ዝንባሌ።

# የሠብአዊ እርዳታ ተደራሽነት ተግዳሮቶች እና የSRM ሚና

## ውስን ዓለም-አቀፍ አሻራ

በሀገሪቱ ሰፊ ክፍሎች ውስጥ ባሉ የደህንነት እጦት ምክንያት እንደ ማያንማር፣ ሶሪያ፣ ዩክሬን እና የመን ያሉ የግጭት አካባቢዎች፣ ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ከአካባቢው/ብሔራዊ ድርጅቶች እና መደበኛ ባልሆኑ ቡድኖች ጋር ሙሉ በሙሉ መገኘታቸውን ሁኔታ አቁመዋል። ብዙ ጊዜ በእነዚህም እና በሌሎች ሁኔታዎች ጋር ተደባልቆ፣ አልፎ ተርፎም በመንግስታዊ ገደቦች የሠብአዊ እርዳታ ተደራሽነት እና በፀጥታ ስጋቶች ክፉኛ ተገድቧል። ይህም የተጐዱ ሰዎችን በመድረስ ላይ ከፍተኛ ተግዳሮቶችን ፈጥሯል፣ በዚህም የተነሳ በርካታ አካባቢዎችን ለዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ተደራሽ እንዳይሆኑ አድርጓል። የጥናት ቡድናችን በዩክሬን ውስጥ የእርዳታ ስራዎች ዘንድ ባለ ሁለት ደረጃ የሠብአዊነት ደህንነት ስርዓት እየመጣ እንዳለ መስክረዋል፦




## የሲቪል-ወታደራዊ እና ግጭትን የማስወገድ ተግዳሮቶች

ግጭትን ማስወገድ – በሰብአዊ ተግባራት እና በሲቪሎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ፣ ከወታደራዊ ተዋናዮች ጋር የመቀናጀት ሂደት ሲሆን – በግጭት ቀጠናዎች ውስጥ ወሳኝ እንቅስቃሴ ነው። እንደ ግጭትን ለማስወገድ የሰብዓዊነት መግለጫ (HNS4D) ያሉ ስልቶችን ለመገንባት ከፍተኛ፣ የተቀናጀ ጥረቶች ቢደረጉም በተዋናዮች መካከል መተማመን አሁንም በጣም በዝቅተኛ ነው፣ እንዲሁም ተሳትፎው ከዓለም-አቀፍ ደረጃ የራቀ ነው፣ ምክንያቱም ብዙ NGO ሠራተኞች ይህንን ማድረግ አደጋ ከመቀነስ ይልቅ የበለጠ አደጋን ይፈጥራል የሚል አመለካከት ስላላቸው ነው።

በተጨማሪም በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ በሠብአዊ እና ወታደራዊ ተዋናዮች መካከል የሚደረገውን ውይይት የሚደግፉ ዘዴዎችን የማስተባበር ድክመቶች (የሲቪል-ወታደራዊ ቅንጅት) NGO አጠቃላይ የማቀናጀት ተግዳሮቶች ላይ አስተዋጾ አበርክተዋል። በተባበሩት መንግስታት የሠብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ(OCHA) የሚመራው የተባበሩት መንግስታት የሠብአዊ መብት ሲቪል-ወታደራዊ ማስተባበሪያ(UN-CMCoord) ከሀብት እጥረት እና አንዳንዴም በይፋዊ የሲቪል-ወታደራዊ መመሪያ እና በመሬት ላይ ባሉ እውነታዎች መካከል ያለው ግንኙነት መቋረጥ ጋር ሲታገል ይታያል። ለእርዳታ ሰጪ ሠራተኞች SRM በውይይቶቹ ውስጥ እንዴት እንደሚገባ የተወሰነ ትኩረት አለ፣ እና በአንዳንድ አውዶች ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የትኛው የተባበሩት መንግሥታት አካል – OCHA ወይም UNDSS – NGO በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ከየትኛው ጋር መተባበር እንዳለባቸው ግልጽነት እናሳ ነው።

## የጋራ ተደራሽነት ተነሳሽነት እና ከSRM ጋር ያልተፈጠረው ትስስር

OCHA ለሠብአዊ እርዳታ ተደራሽነት የትኩረት ነጥብ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ይህንን ሚና መደበኛ ለማድረግ እና ለማጠናከር ጥረት አድርጓል፤ ይህም ሚና በአገር አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም የትብብር ጥረቶችን፣ በሰብአዊ ተደራሽነት ቡድኖች ውስጥ ቅስቀሳ፣ ተግባራዊ ስልቶች እና ድርድር ጥረቶችን ጨምሮ "ቢያንስ አነስተኛ የአገልግሎት ጥቅል ተደራሽነትን" ማቅረብን ያካትታል። እነዚህ ጥረቶች በአብዛኛው ሠብአዊነት ተዋናዮች ዋጋ የሚሰጣቸው ናቸው፤ በተለይም በዚህ የስራ መስክ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም ሄይቲ እና ዩክሬን የOCHA አመራር ለሰራው ስራ ምስጋና ይገባዋል።

ነገር ግን፣ እነዚህ ተደራሽ የስራ ቡድኖች በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ የሉም፣ ቢኖሩም ጥናቱ ከSRM ሰራተኞች ጋር ግንኙነት አለመኖሩን አረጋግጧል። ይህ ከSRM እና በተደራሽነት ተግባራት መካከል ያለው ልዩነት አንዳንድ ጊዜ በግለሰብ ድርጅቶች ውስጥ ይንጸባረቃል፣ ይህም በSRM ቡድኖች እና በፕሮግራም ሰራተኞች መካከል በተደራሽነት ተግባራት ላይ በትብብር ከሚሰሩ ይልቅ ውጥረት ሊኖር ይችላል። በSRM ስልቶች መካከል የተሻለ ውህደት እና በተደራሽነት ላይ መስራት ሁለቱንም ሊያሻሽል ይችላል።

## ተደራሽነት እና ተቀባይነት

ሌላው ተደራሽነትን የመመልከቻ መንገድ በመጨረሻው ተቀባይነትን ለማግኘት ተከታታይ ጥረቶች ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆዩ NGO ከአከባቢው ጋራ መዋሃድ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ከማህበረሰቦች እና ከባለሥልጣናት ጋር የተገነባው መተማመን ፈታኝ በሆኑ ቦታዎች ላይ ለቀጠለው ተደራሽነታቸው ቁልፍ እንደሆነ ይመሰክራሉ። ለብዙዎች፣ ተቀባይነት ማግኘት የSRM አቀራረብ ዋና ትኩረት ሆኖ ይቀጥላል። ነገር ግን በአንዳንድ የግጭት አካባቢዎች ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ተዋጊዎች የሠብዓዊ ድርጅቶችን ገለልተኛ ተዋናዮች አድርገው የማይመለከቷቸው እና ለሠብዓዊ ሠራተኞች በዓለም-አቀፍ የሰብዓዊነት ሕግ መሠረት የተጠበቀ ሁኔታቸውን የማይሰጡበት፣ ተቀባይነት ያላቸው ስልቶች ደህንነቱ የተጠበቀ መዳረሻ ለማግኘት በቂ አይደሉም። በአሁኑ ጊዜ በሠብአዊ ዘርፍ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ሰፋ ያለ ውይይት በገለልተኝነት እና ከወገነተኝነት የጸዳ፣ ሰብአዊ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ተቀባይነት ብቻ ሳይሆን እንደ ማያንማር እና ዩክሬን ካሉ ከተጨቆኑ ህዝቦች ጋር በመተባበር ላይ የተመሰረተ አቀራረቦች ይበልጥ ተገቢ መሆናቸውን ያመላክታል።

# SRM እና ግለሰቡ

ብዙ ባለሙያዎች በSRM ውስጥ የብዝሃነትን እና የአካታችነትን አስፈላጊነት በሁለት መልኩ ይናገራሉ፤ በመጀመሪያ፣ የማንነት ባህሪያት የእርዳታ ሠራተኛ ግለሰብ አደጋ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ፤ በሁለተኛ ደረጃ የደህንነት ሠራተኞችን መገለጫዎች ራሳቸው የተለያየ ማድረግ።

## በSRM የሰዎች ሚና

በጥናት ቡድኑ እና በቃለ መጠይቅ ተደራጊዎች ከተለዩት ዋና ዋና አዝማሚያዎች መካከል በSRM የሥራ መደቦች ውስጥ በተሰማሩ ባለሙያዎች መገለጫዎች ውስጥ እያደገ ያለ ልዩነትን ነው። በአጠቃላይ፣ ከቀደምት አመታት በበለጠ ማንነት የሚከተሉት የማንነት መገለጫዎች እና የደህንነት ሠራተኞች ክህሎት ስብስቦች ያሉ ይመስላሉ፦

- የሠብአዊነት ዳራዎች
- በስተደቡብ ከሚገኙ የአለም ሀገራት የመጡ ግለሰቦች(ኋላ ቀር ከሚባሉ አገራት)
- ሴቶች
- ከሌሎች ሰዎች ጋር በብቃት መግባባት የሚችሉ ግለሰቦች

## በሰው ላይ ያተኰረ የደህንነት አቀራረብ

በSRM አስተሳሰብ ውስጥ እየተፈጠረ ያለው መግባባት የአንድ የእርዳታ ሠራተኛ የግል ደህንነት የሚነካው በዕርዳታ ሠራተኛው በሚሠራበት ቦታ፣ በሚጫወተው ሚና እና ድርጅት እና ማንነት (ከሌሎች ጋር ባለው መስተጋብር ያለ ማንነት እንደ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ ጎሳ፣ እና ዜግነት) ተጽዕኖ ስር ያድራል። በSRM ውስጥ አስተሳሰብ ያላቸው መሪዎች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በድርጅታዊ SRM አቀራረቦች ውስጥ በማንነት ላይ የተመሰረቱ አደጋዎችን ለማካተት ያለመውን" በሰው ላይ ያተኰረ" የደህንነት አቀራረብን ይደግፋሉ።

**በመሰረቱ፣ በሰው ላይ ያተኰረ አቀራረብ ከግለሰብ የስጋት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ ተገቢውን የአደጋ ስጋት ቅነሳ እርምጃዎችን ማስቀመጥ እንጂ በግለሰብ ማንነት መገለጫዎች ምክንያት ከሰራተኞች እድሎችን መቀነስ አይደለም የሚል ነው።**

በዚህ ጥናት ውስጥ ያሉ ብዙ የደህንነት ሠራተኞች አሰራሩን አውቀው ይደግፋሉ፤ ነገር ግን በድርጅታቸው የSRM መዋቅር ውስጥ እንዴት ሊፈቱት እንድሚችሉ ግን እርግጠኛ አይደሉም። በዚህ ቦታ እየተካሄዱ ያሉ አንዳንድ ቁልፍ ውይይቶች እዚህ ተዘርዝረዋል፦

### የግለሰባዊ አደጋ ግምገማዎች

- የግለሰባዊ የአደጋ ግምገማዎች በተለይ ለሰራተኞች ከጉዞ በፊት ግምገማዎች ሲደረጉ በሰው ላይ ያተኰረ አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ ቁልፍ ዘዴ ነው፣ ነገር ግን ተደጋጋሚ የሰራተኛ ስምሪት ላላቸው ድርጅቶች እና በሀገር ውስጥ ትልቅ ቡድን ላሉት ድርጅቶች እውን ሊሆን የማይችል ነገር ነው።

### መረጃን ማጋራት

- አንዳንድ ድርጅቶች በአጠቃላይ ለሰራተኞቻቸው አደጋዎችን የማሳወቅ መንገድን (ለምሳሌ፡ በአንዳንድ ሀገራት ስላለው የአደጋ ተጋላጭነት መረጃን ሌዝቢያን፣ግብረሠዶም፣ ሁለት ፆታ ፍላጎት ያለው፣ፆታውን ያሰቀየረ ሰራተኞች በማቅረብ) እና ሰራተኞች ከፈለጉ ስጋታቸውን እንዲያነሱ በማበረታታት በመሳሰሉት ተከትለዋል።
- ግለሰቦች በመረጃ ላይ የተመሰረተ የግል ደህንነት ውሳኔዎችን እንዲወስኑ የሚያስችል በቂ መረጃ የሚሰጥ ዝርዝር ስምምነት ሂደት መወሰን አንድ ድርጅት በሰው ላይ ያተኰረ አቀራረብ እንዲጠቀም ያስችለዋል እንዲሁም ድርጅቱ የጥንቃቄ ግዴታውን እንዲያሟላ ይደግፋል።

### የመድልዎ ስጋት

- ብዙ የደህንነት ባለሙያዎች ከደህንነት ጋር በተያያዙ የማንነት ጉዳዮች ላይ መሳተፍ መቼ የ"ድጋፍ" ዓይነት ነው እና መቼ "አድልዎ" ነው በሚል አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚገኙ ተናግረዋል።
- ነገር ግን፣ በተቃራኒው "አትጠይቅ፣ አትናገር" የሚለው አካሄድ፣ በግል ተጋላጭነት ዙሪያ የሚደረጉ የደህንነት ውሳኔዎች በዘፈቀደ እና በግለሰብ ውሳኔ ሰጪዎች እምነት እና ጭፍንነት ላይ የተመሰረቱ የመሆኑን ስጋት ይጨምራል።

### የተቋማዊ አሠራር ጥቅሞች

- ተቋማዊ እና ስልታዊ አቀራረብ አድልዎ እና ኢፍትሃዊነትን በመቀነስ ስለተለያዩ አደጋዎች ግልጽነትን እና የመወያየት ባህልን ያዳብራል።

### በሰው ላይ ያተኰረ የደህንነት አቀራረብ ተግባራዊ ምሳሌዎች

- በስልጠና፣ የአደጋ ስጋት ግምገማ፣ የአደጋ ቅነሳ እርምጃዎች እና የጉዞ መመሪያ ሰነዶች ላይ በማንነት የሚደርስ የአደጋ ስጋትን ማካተት።
- በማንነት ላይ የተመሰረተ የአደጋ ስጋቶች እና ድርጅታዊ ድጋፍን በተመለከተ አጠቃላይ ግንኙነት መኖር።

# ማጠቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች (1/2)

የእርዳታ ድርጅቶች የደህንነት አደጋ ስጋቶችን በመቆጣጠር ረገድ ያሳዩት ትልቅ እድገት፣ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ የቀውስ ሁኔታዎች ውስጥ ስራቸውን በመቀጠላቸው በመሆኑ በሰብአዊ እርዳታ ሰጪዎች ዘንድ እውቅና ያለው ነው። የተገኘውን እድገት ለማጠናከር የሚቀጥለው የጥረቶች ምዕራፍ የSRM የአፈጻጸም አቅሞችን እና ብቃቶችን ለሁሉም የሠብአዊነት ቦታ ላይ በማስፋት ላይ ማተኮር አለበት። በዓለምአቀፍ እና በአካባቢያዊ NGO መካከል ያለውን ጉልህ ልዩነት ለማጥበብ መሥራት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ የሚመጡ የደኅንነት ስጋቶችን ማስተካከል፣ የበለጠ ወደ ፊት መመልከት እና በSRM ልምዶች ውስጥ በሰው ላይ ያተኰረ አቀራረብን ማጐልበት ይበልጥ ፈታኝ በሆኑ አካባቢዎች ውስጥ እርዳታ ለማድረስ ቁርጠኛ የሆኑትን በተሻለ ሁኔታ ይከላከላል።

## ምክረ ሃሳቦች

### ከአዳዲስ አደጋዎች እና ስጋቶች ጋር መላመድ

- የአካባቢያዊ ሁኔታዎችን እና የአደጋ ደረጃዎችን በመለየት እና በማላመድ ሂደት ውስጥ የSRM ስርዓቶች እና ሰራተኞች አመራርን በማረጋገጥ የተዘመኑ እና ምላሽ ሰጪ የአደጋ ስጋት ግምገማ ሂደቶችን ማሰቀጠል።
- አዳዲስ የፈጠራ አስተሳሰቦችን እና ድርጅታዊ የመቋቋም አቅምን ለማነሳሳት ቡድኖች ሊሆኑ የማይችሉ ነገር ግን ተጽእኖ ስላላቸው ክስተቶች ሃሳብ በሚያፈልቁበት፣ ወደፊት የሚመለከቱ ትንታኔዎች የሚሰጡበት’ የቤት ውስጥ የውይይት ልምምዶችን ለማዳበር ማሰስ።
- ለአደጋ ስጋት ግምገማ እና ሁኔታዎች ትንተና የግብአት ወሰንን በማስፋት፣ ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጡ ሰራተኞችን እና በሁሉም የድርጅቱ እርከኖች የተውጣጡ ሰራተኞችን በማሰባሰብ ስለሁኔታው የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ።
- የተሳሳቱ መረጃዎችን እና የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን ጨምሮ አዳዲስ ስጋቶችን እና አደጋዎችን ለመገምገም ተገቢውን የችሎታ ስብስቦችን እና የትኩረት ነጥቦችን መለየት እና በSRM፣ በአይቲ እና በግንኙነት ሠራተኞች መካከል የድርጅት ኃላፊነቶችን ግልጽ ማድረግ።

### የበለጠ ስነምግባር የተላበሰ እና ፍትሃዊ በሆነ አጋርነት SRMን አካባቢያዊ ማድረግ

- ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች፣ ከማስተላለፍ ይልቅ የደህንነት አደጋ ስጋቶችን ከአከባቢው እና ከብሔራዊ አጋሮች ጋር እንዲጋሩ ማበረታታት። ይህም ለጋሾች የSRM የትብብር እቅድ ማስረጃ እና ለማንኛውም በሶስተኛ ወገን አጋሮች የተደረገ ድጋፍን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያሳዩ በመጠየቅ ሊሳካ ይቻላል።
- ውሎች ከመፈረማቸው በፊት የSRM ጉዳዮች በፕሮግራም ተግባራት ውስጥ መካተታቸውን ለማረጋገጥ የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደር ሰራተኞችን ከአጋሮች ጋር የሚደረግ ፕሮጀክት ቀረጻ ወቅት ማካተት።
- የመልካም አጋርነት መርሆዎችን ፍትሃዊነት፣ ግልፅነት፣ የጋራ ተጠቃሚነት፣ አብሮነትን እና ኃላፊነትን ድርጅታዊ አስተሳሰብን ከ”አደጋን ማሸጋገር” ወደ “አደጋን መጋራት” አስተሳሰብ ለማሸጋገር ስራ ላይ ማዋል።
- በፕሮግራም በጀቶች ውስጥ የደህንነት ወጪዎችን ጨምሮ በቂ የስራ ማስኬጂያ ወጪዎችን በማቅረብ እና የተግባር ለውጦችን የመቀበል አቅምን በመገንባት እንዲሁም ከአቅም በላይ የሆኑ አደጋዎች እና አስከፊ ክስተቶች ተጠያቂነትን የሚያስወግድ አንቀጾችን በውሎች ውስጥ በግዳጅ እንዲካተቱ በማድረግ አስቀድሞ የተሰጡ የፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ምክሮችን ተግባራዊ ማድረግ።

### ቅንጅትን መደገፍ እና የሸፉን ክፍተቶችን መሙላት

- ለSRM አቅምን ለማካተት እና ለማዳበር እንዲሁም የSRM ዙሪያ ለማሰባሰብ ነባር ሀገራዊ እና አካባቢያዊ ማስተባበሪያ መድረኮችን እና/ወይም አዳዲስ የአካባቢ ተነሳሽነቶችን መደገፍ። ይህም ዓለም-አቀፍ አካላት SRM እና ሁሉንም የአካባቢው ተዋናዮች የመቀናጀት ፍላጎት ማስተናገድ እንደማይችሉ በመገንዘብ እንዲሁም በአገር ውስጥ ለሚመሩ አካላት አሁን በሰራ ላይ ካሉ የቅንጅት መድረኮች ጋር ለማጠናከር እና ለማገናኘት ጥቅሞች እንዳሉት በመገንዘብ ነው።

# ማጠቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች (2/2)

## በስራ ላይ ያለውን የSRM አካላት በደንብ ማጥራት እና ማስፋፋት

- ለበለጠ ስልታዊ የደህንነት አደጋ ጉዳዮች ክትትል፣ የአካባቢያዊ እና ብሔራዊ ድርጅቶች የአደጋ ክትትል ስርዓቶችን መደገፍ እና ማጠናከር።
- የአካባቢያዊ እና ብሔራዊ ሠራተኞች እና ድርጅቶች የሥልጠና ተደራሽነትን እና አግባብነትን ማሻሻል፣ በተለይም ሥልጠናው ለሚያስፈልጋቸው በርካታ የአገር ውስጥ የእርዳታ ሠራተኞችን ማስተናገድ የሚችል ቀጣይ፣ አግባብነት ያላቸው የሥልጠና እድሎችን በአገር ውስጥ ቋንቋዎች በማሰባሰብ ቢሆን ይመረጣል።
- የሰራተኞችን ሁለንተናዊ ደህንነት እና የአእምሮ ጤናን ችግር ለመፍታት የአካባቢውን ባህል በጠበቀ መልኩ የአዕምሮ ጤና ድጋፍ እና ደጋፊ የስራ አካባቢን በመፍጠር ድጋፍ ያድርጉ።

## የSRMን የተሻሻለ የሠብአዊ እርዳታ ተደራሽነትን ለማሳደግ እንጂ እንቅፋት ለመሆን አለመጠቀም

- ቀጣይነት ባለው የተደራሽነት ተነሳሽነት እና ድርድሮች ውስጥ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስልቶችን እና የSRM እውቀትን ለማካተት ለማስቻል የደህንነት አደጋ ስጋት አስተዳደርን ወደ ተደራሽነት ተነሳሽነት እና በድርጅቶች ውስጥ እና በድርጅቶች ውስጥ እያደገ የመጣውን ተደራሽነት እና ደህንነትን ለማስቀረት። ይህ SRM የፕሮግራም አቅርቦትን የማሻሻል እንጂ እንቅፋት አለመሆኑን እንዲሁም በራሱ ፍጻሜ እንዳልሆነ አበክሮ ማሰገንዘብን ይጠይቃል።
- ከመንግሥታት ጋር በመተማመን እና ተጠያቂነት ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍ በጋራ ስትራቴጂ አማካኝነት ግጭቶችን በማስወገድ ረገድ ድክመቶችን መፍታት።

## በሰው ላይ ያተኰረ አቀራረብን ማስፋፋት

- በSRM ሥርዓቶች ውስጥ በማንነት ላይ የተመሰረቱ አደጋዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ተቋማዊ ማድረግ፣ ይህ በአሁኑ ጊዜ ካለው የበለጠ የተስፋፋ እና የተለመደ የአደጋ አስተዳደር እና ቅነሳ አቀራረብ እንዲሆን ማድረግ።
- የተለያዩ ማንነቶችን እና የግል ስጋት መገለጫዎችን የሚደግፍ ድርጅታዊ ባህልን መፍጠር፣ በዚህም የተለያዩ ማንነቶችን የሚያሰተናግድ የሰራ አካባቢን መፍጠር።
- በSRM እና በሰብአዊ ፕሮግራሞች እና መርሆዎች ውስጥ የክህሎት እና የመረዳት ሚዛን ያላቸው የተለያዩ የደህንነት ባለሙያዎች ስብስብን በማረጋገጥ የSRM ሰራተኞችን የማንነት መገለጫዎችን የበለጠ ማባዛት።